# የዓቂዳ መሠረቶች

ተርጓሚው ዓብዱ ናስር ዓብዱላሂ አሕመድ

አሳታሚው ሣዕዋ ገሬስ

የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

Kingdom of Saudi Arabia
The Cooperative Office for call and Guidance
to Communities at Al Ma'azar & Um Al-Hammam
Under the Supervision of the Ministry of Islamic Affairs
Endowment Guidance & Propagation
Tel: 4826466 - Fax: 4827489 - P.O.Box: 31021 Riyadh: 11497

# የአቂዳ መሠረቶች

ተርጓሚው አብዱልናስር አብዱላህ አህመድ

አሳታሚው ዳዕዋ ፕሬስ
የመ.ሳ.ቁ 80324
ስ.ቁ. 183184

እርግት በምርጥ ሙስሊም ምሁራን

ጥር 1986
አዲስ አበባ

مؤسسة الدعوة للنشر والإعلام

All Rights Reserved
የ ተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

# መግቢያ

ምስጋና ለአላህ ይገባው። እዝነትና ሰላም ለነቢያችን ሙሐመድ ለቤተሰቦቻቸውና ለሰሓቦቻቸው ይድረስ።

ሙስሊሞች ሆይ! ኢስላም ሕይወትን በየፈርጁ የሚመራ የተሟላ እንከንና ጉድለት የለለው ሐይማኖት ነው። ምንጩም ቁርዓንና ሐዲስ ነው።

ሙስሊም መሆንም በኢስላም ጓዳና ላይ በመጓዝ እንጂ በስላም ብቻ አይደለም። የኢስላም ቀለበት ውስጥ መግባት: ለአላህ እጅ መስጠት ለፍቃዱና ለትዕዛዙ ፍፁም ተገዥና ታዛዥ መሆን ማለት ነው።

ሙስሊሞች ሆይ! የኢስላም ምሰሶውና የጀርባ አጥንቱ አቂዳ ነው። አቂዳችን በቁርዓን በሐዲስ ላይ የተመሠረተ የተስተካከለና ያማረ ካልሆነ የምንሰራው ሥራ በሙሉ ከጥያቄ ውስጥ ይወድቃል። ስለዚህ አቂዳችንን የምናስተካክለው በቁርዓንና በሐዲስ የታዘዙትን በመሥራት በመተግበር ሲሆን የተከለከሉትን በመከልከል ነው። የሙስሊሞች አንድነትም የሚገነባውና የሚመሠረተው በአቂዳ ላይ ነው።

በጀሚአት እህያ ምንሓጅ አል-ሱ-ን-ና(የ.ከ) “ፈንዳሜንታልስ ኦፍ አቂዳ” በሚል ርዕስ በእንግሊዘኛ ከተዘጋጀው መጽሐፍ ወደ አማርኛ የተመለሰ ነው።

መፅሐፉ የአቂዳን ምንነት በማሳየቱ በኩል ትልቅ አስተዋፅኦ የሚያበረክት መሆኑን ብዙ ሙስሊም ምሁራን በማረጋገጣቸው ባማረና በተሟላ ሁኔታ እነሆ ለሁለተኛ ጊዜ ለማሳተም በቅተናል።

መጽሐፉም የተሳሳተ መልዕክት እንዳይኖረው ሺህ ሰዒይድ አህመድ በማረም ረድተውኛል:: አላህ ይህንን መልካም ሥራ ይቀበላቸው።

ቀጥተኛውን መንገድ ምራን: የነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክ ላቸውን: በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ(ምራን: በሉ)። አል-ፋቲሐህ(1:6-7)

አብዱልናስር አብዳላህ አህመድ

# የአቂዳ መሠረቶች

ጥ1. አላህ ለምን ፈጠረን?

መ. አላህ የፈጠረን ለእሱ ፍጹም ተገዢና ታዛዥ እንድንሆንለት ነው። በእሱ ማንንም፣ ምንንም እንዳናጋራ ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وَمَاخلَقتُ الجِنَّ وَالإنسَ إلاَّ لِيعْبُدونَ ﴾ . سورة الذاريات

*ጋኔንንና ሰውንም:- ሊገዙኝ እንጂ ለሌላ አላፈጠርኳቸውም። (51:56)*

ሐዲስ

( حَقُّ الله على العِبَادِ أن يَعبُدُوه وَلا يُشرِكُوا به شيئاً ) . رواه مسلم

የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) *አላህ በባሮቹ ላይ ያለው መብት እሱን በብቸኝነት እንዲያመልኩትና ማንንም፣ ምንንም እንዳያጋሩበት ነው።* ሲሉ ተናግረዋል። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ጥ2. ኢባዳ ምንድን ነው?

መ. ኢባዳ (ፀሎት): (አምልኮት) ለአላህ ውዴታ ተብለው የሚከናወኑ መልካም ተግባሮችን፣ ሥራዎችንና ንግግሮችን በሙሉ የሚያካትት ነው። ለምሳሌ ፀሎት፣ ሰላት፣ ምፅዋት እና ሌሎችንም በጎ ሥራዎች ያጠቃልላል።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ قُل إنَّ صلاتي ونُسكي وَمحيايَ وَمَماتي لله ربِّ العالَمينَ ﴾
سورة الأنعام .

*ስግደቴ፡ መገዛቴም፡ ሕይወቴም፡ ሞቴም፡ ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው በል።(6:162)*

**ሐዲስ**

قَالَ رَسولُ الله صَلَى الله عَلَيه وَسَلم : قَالَ الله تعالى : وَمَاتقَرَّبَ إلَيَّ عَبدِيَ بشيء أَحَبَّ إلَيَّ مما افتَرَضته عليه . حديث قدسي رواه البخاري .

**የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ)** *አላህ ባሪያዬ ወደ እኔ ከሚቀርብ ባቸው ተግባራት መካከል በግዴታ እንዲዘዝኩት ይበልጥ የተወደደ የለም።* ይላል ሲሉ ተናግረዋል። (ቡኻሪ)

**ጥ3. አላህን እንዴት እንገዛው?**

**መ. አላህን የምንገዛው እሱ ባዘዘንና መልክተኛው (ሰዐወ) ባስተማሩን መሠረት ነው።**

**ቁርአን እንዲህ ይላል:-**

﴿ ياأيها الذين آمنوا أطيعوا الله وأطيعوا الرسول ولا تُبطلوا أعمَالَكم ﴾ سورة محمد .

*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ፡ መልእክተኛውንም ታዘዙ፡ ሥራወቻችሁን አታበላሹ:: (47:33)*

وَقَال صَلى الله عليه وسلم : مَنْ عَمِلَ عَمَلاً ليس عليه أمرنا فهو رَدّ . رواه مسلم .

**የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ)** *የእኛ ፍቃድ ያልሆነን ነገር ያከነወነ ሰው ተግባሩ ውድቅ ነው።* ሲሉ ተናግረዋል። (ሙስሊም)

**ጥ4. አላህን በፍርሃት በተስፋ መገዛት አለብን?**

መ. አዎ! አላህን መገዛት ያለብን በፍርሃትና በተስፋ መሆን አለበት። የአላህን ቁጣ: ቅጣትና ቅሬታ በመፍራት እሱ ከሚጠላቸው ከማናቸውም መጥፎ ተግባሮች መቆጠብና ራሳችንንም መከልከል አለብን። እንደዚሁም እሱን ስንገዛ በውዴታ፣ በፍቅርና በቆራጥነት መሆን አለበት። በቅርቡና በወዲያኛው ዓለም የሱን ችሮታና ምህረት ለማግኘት በሙሉ ልብ ማመስገን አለብን።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ تَتَجافَى جُنُوبهم عَنْ المَضَاجِع يَدعُونَ رَبَّهم خَوفاً وَطَمَعاً ﴾
سورة السجدة .

*ጎኖቻቸውን ለመፍራትና ለመከጀል የሚጠሩት ኾነው ጎኖቻቸው ከመጋደሚያ ስፍራዎች ይራራቃል። (32:16)*

ሐዲስ

وَقَال صَلَّى الله عَلَيهِ وَسَلَّم : أسْأَلُ الله الجَنَّةَ وأعُوذُ بِه مِنَ النَار .
رواه أبو داود .

የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) *አላህ ጀነትን እንዲሰጠኝ እማፀነዋለሁ: ከእሳትም እንዲያድነኝ እለምነዋለሁ።* ብለዋል። (አቡዳውድ)

ጥ5. ዒህሳን ምንድን ነው?

መ. አላህን ስትገዛ እኔ ባላየውም እሱ ያየኛል ብለህ ፍርሃት በተመላበት መንፈስ የምታከናውነው አምልኮት (ዒባዳ) ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ الَّذِي يَرَاكَ حِينَ تَقُوم وَتَقَلُّبَك فِي السَّاجِدِين ﴾ سورة الشعراء .

*በዚያ ለበላት በምትቆም ጊዜ፡ በሚያይህ፡ በሰጋጆች ውስጥ መዘዋወርህንም፡ (በሚያየው ጌታህ ላይ ተጠጋ)።*(26:217-216)

ሐዲስ

قَالَ صَلَّى اللهُ عَلَيهِ وَسَلَّم : الإحسَانُ أن تَعبُدَ اللهَ كأنَّكَ تَراهُ ، فإنْ لَمْ تَكُنْ تَراهُ فإنَّهُ يَرَاكَ . رواه مسلم .

የአላህ መልእክተኛ(ሰዐወ) *ቲህሳን ማለት አላህን ስትገዛ ልክ ከፊት ለፊትህ እንደምታየው ሆነህ ነው። አንተ ባታየውም እሱ ያይሃልና።* ሲሉ ተናግረዋል። (ሙስሊም)

ጥ6. አላህ መልእክተኞቹን ለምን ላካቸው?

መ. አላህ መልእክተኞቹን የላከበት ምክንያት ሰዎች አንድና ብቸኛ የሆነውን ጌታ- አላህን እንድገዙ ጥሪ እንዲያደርጉና ከሽርክ(ማጋራት) እንዲነፁ ለማድረግ ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وَلَقَدْ بَعثنَا فِي كُلِّ أمَةٍ رَسولاً أن اعبُدوا اللهَ وَاجتَنِبوا الطَّاغُوت ﴾ سورة النحل.

*በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ አላህን ተገዙ፤ ጣኦትንም ራቁ: በማለት መልዕክተኛን በእርግጥ ልከናል።(16:36)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى اللهُ عَلَيهِ وَسَلَّم : وَالأنبِيَاءُ إخوَةٌ .. وَدِينهُم وَاحِدٌ . رواه البخاري ومسلم .

የአላህ መልክተኛ (ሰዐወ) *ነቢያት ወንድማማቶች ናቸው፤ ሃይማኖታቸውም አንድ ወጥ ነው።* ብለዋል። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ጥ7. የተውሂድ አል ሩቡቢያ ትንታኔ ምንድን ነው?

መ. ተውሒድ አል ሩቡቢያ ማለት የአለም ፈጣሪ፡ መጋቢ፡ ተንከባካቢ አንድ አላህ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ፣ አስተዳዳሪውም ጠቃሚውም ጎጂውም እሱ ብቻ መሆኑን ማመን ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ الحَمدُ لله رَبِّ العَالِمِين ﴾ سورة الفاتحة.

*ምስጋና ለአላህ ይገባው: የአለማት ጌታ ለሆነው። (1:1)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : أَنْتَ رَبُّ السَّمٰوَاتِ والأَرضِ
البخاري ومسلم .

የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) *ጌታዩ ሆይ አንተ የሰማያትና የምድር ጌታ የሆንከው። ሲሉ በዱአዐቻቸው ተናግረዋል።* (ቡኻሪና ሙስሊም)

ጥ.8 ተውሒድ አል ዒባዳ ምንድን ነው?

መ. ተውሒድ አል ዒባዳ ማለት በአላህ ጌትነትና አንድነት ሙሉ በሙሉ አምኖ ዒባዳ ወይም አምልኮት የተባለውን በሙሉ ለሱ ብቻ ፍፁም ማድረግ ነው። ይህም የአምልኮት ዘርፍ የሆኑትን እንደ መስዋእት፣ መስገድ፣ መማፀን፣ ዱዓዕ እና የመሳሰሉትን የዒባዳ ዘርፎች ሲያጠቃልል: እነሱም የአላህ የግሉ መብት መሆናቸውን አውቆ ለእርሱ ብቻ ማዋል ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وَإِلٰهُكُم إِلٰهٌ وَاحِدٌ لاَ إِلٰهَ إِلاَّ هُوَ الرَّحمٰنُ الرَّحِيم ﴾ سورة البقرة.

*አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ (እርሱ) እጅግ በጣም ርህሩህ አዛኝ ነው። (2:163)*

ሐዲስ

قَالَ صلى اللهُ عَليه وَسَلَّم : فَلْتَكُن أَوَّلَ مَائدْعُوهم إِلَيهِ ، شَهادَةُ أَنْ لاَ إِلَهَ إِلاَّ الله ... الخ . البخاري ومسلم .

የአላህ መልክተኛ(ሰዐወ) *ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ማሳወቅ የመጀመሪያው ጥሪ ነው። ሲሉ ተናግረዋል።* (ቡኻሪና ሙስሊም)

ጥ9. ተውሂድ አል አስማዕ ወሲፋት ምንድን ነው?

መ. ተውሂድ አል አስማዕ ወሲፋት ማለት ፍጹም በሆነ መንገድ አላህ አንድና ብቸኛ ጌታ መሆኑን ማረጋገጥ: ማመን። በአላህ በቁርአን እንደተጠቀሰውና በመልእክተኛው(ሰዐወ) በሐዲስ በተጠቀሱት የአላህ ችሎታዎች: ባሕሪያትና ስሞች በትክክል ለእርሱ መጥሪያ ማወደሻ ማድረግ ነው። በእነዚህ ስሞችም ከናምን በፍጡር ስም ሳናመሳስል: ለእሱ መጥሪያ: ብቻ ማዋል አለብን። በተጨማሪም ስሞቹንም ትርጉም አልባ ያለማድረግና ያለማዛባት በቀጥታ በቁርአንና በሐዲስ በተጠቀሱት መሠረት በተገቢው ቦታ ለሱ ብቻ ማድረግ ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ لَيسَ كَمِثلِهِ شَيءٌ وَهوَ السَمِيع البَصير ﴾ سورة الشورى .

*የሚመስለው ምንም ነገር የለም፤ እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው። (42:11)*

ጥ10. ጣዖት ምንድ ነው?

መ. ጣዖት ማለት ሰዎች ከአላህ ሌላን እንዲያመልኩ የሚጋብዝ ሸይጣን ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ فَمَن يَكفُر بالطَّاغوتِ وَيؤمِن بالله فَقَد استَمسَكَ بالعُروة الوثقى لا انفصَامَ لَها ﴾ سورة البقرة .

*በጣኦትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው፡ ለርሱ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በርግጥ ጨበጠ፤(2:256)*

ጥ11. አላህ የት ነው?

መ. አላህ ከሰማያት በላይ በዙፋኑ ላይ ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ الرَّحمٰن عَلَى العرش استَوى ﴾ سورة طه .

*አልረሕማን በአርሹ ላይ ተደላደለ።(20:5)*

ሐዲስ

وقَالَ صَلّى الله عَليه وَسَلَّم : إنَّ الله كَتَبَ كِتَاباً .. فَهوَ عنده فَوقَ العَرش .البخاري ومسلم .

የአላህ መልክተኛ (ሰዐወ) *አላህ መፅሐፍ ፅፎዋል፤ እርሱም ከአርሽ በላይ በሱ ዘንድ ይገኛል። ብለዋል።* (ቡኻሪና ሙስሊም)

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ إذهَبَا إلَى فِرعَونَ إنهُ طَغى . فَقُولاَ لَهُ قَوْلاً لَيِّناً لَعَلَّهُ يَتَذَكَّر أو يَخشَى . قَالاَ : رَبَّنَا إنَّنَا نَخافُ أنْ يَفرطَ عَلينَا أو أنْ يَطغَى . قَالَ : لاَ تَخافَا إنَّني مَعَكُمَا أسمَعُ وَأرى ﴾ سورة طه .

*ወደ ፈርኦን ሂዱ፤ እርሱ ወሰን አልፏልና እርሱም ይገሰፅ ወይም ይፈራ ዘንድ፤ ለርሱ ልዝብን ቃል ተናገሩት። ጌታችን ሆይ!*

*እኛ በኛ ላይ ክፉን በመስራት መቸኮሉን ወይም ኩራትን መጨመሩን እንፈራለን ፣ አሉ ፡- (አላህም) አለ ፡- አትፍሩ፤ እኔ በርግጥ ከናንተ ጋር ነኝና እሰማለሁ፤ አያለሁም።(20:43-46)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : إنكُمْ تَدعون سَميعاً قَرِيباً وَهُوَ مَعَكُم

رواه مسلم .

የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:- *እናንተ ሰሚና ቅርብ ለሆነ ጌታ ነው የምትፀልዩት፤ እርሱም ከናንተ ጋር ነው።* (ሙስሊም)

ጥ13. የተውሂድ ጥቅም ምንድን ነው?

መ. የተውሂድ ጥቅም በወዲያኛው አለም ከአላህ ቅጣት ምህረት ለማግኘትና በዚህች ዓለም ደግሞ ቀናውን መንገድ ለመከተል: እና ከወንጀሎች ሁሉ ነፃ ለመሆን ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ الَّذِينَ آمَنُوا وَلَم يَلبَسُوا إيمَانَهُم بِظُلم أولَئِكَ لَهُم الأمنُ وَهُم مُهتَدُون ﴾ . سورة الأنعام

*እነዚያ ያመኑና እምነታቸውን በበደል (ሽርክ) ያልቀላቀሉ፤ እነዚያ ለነርሱ ፀጥታ አላቸው፤ እነሱም የተመሩ ናቸው።(6:82)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : حَقُّ العِبَادِ عَلَى الله أنْ لايُعَذِّبَ مَن لا يُشرِكَ به شيئاً . البخاري ومسلم .

የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) *ባሪያዎቹ በጌታቸው ዘንድ ያላቸው መብት በሱ እስካላጋሩበት ድረስ እንደማይቀጣቸው ዋስትና መሰጠቱ ነው፤ ቢሉ ተናግረዋል።* (ቡኻሪና ሙስሊም)

ጥ14. መልካም ሥራ ተቀባይነት እንዲያገኝ መሟላት ያለባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

መ. መልካም ሥራ በአላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሶስት ነገሮች መሟላት አለባቸው። እነሱም:-

1. በአላህ አንድነትና ብቸኛ አምላክነት በትክክል ማመን።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ إنَّ الذينَ آمنُوا وَعملوا الصَالِحَاتِ كَانت لَهُم جَنَاتُ الفِردَوسِ نُزُلاً ﴾ . سورة الكهف .

እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችንም የሠሩ፣ የፊርደውስ ገነቶች ለነሱ መስፈሪያ ናቸው። (18:107)

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : قُل آمَنتُ بالله ثَمَ استَقِم . رواه مسلم .

የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:- *በአላህ አመንኩ በል፣ በፍቃዱም ቀጥ በል።*(ሙስሊም)

2. ሥራው የጠራና ከልብ የመነጨ መሆን፣ ይህም ማለት የሚሰራው መልካም ስራ ለአላህ ውዴታ ተብሎ መሆን እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው። ሥራው ሰዎችን ለማስደሰት፣ ከሰው ፊት አክብሮትንና አድናቆትን ለማትረፍ ተብሎ የተሰራ (የይስሙላ ስራ) መሆን የለበትም።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وَمَا أمِروا إلاّ ليعُبدوا الله مُخلصين له الدين حُنَفَاءَ ﴾ سورة البينة .

*አላህን፡ ሀይማኖትን ለርሱ ብቻ አጥሪዎች፡ ቀጥተኞች ሆነው ሊገዙት፡(98:5)*

3. ሥራውም መከናወን ያለበት የአላህ መልእክተኛ(ሰዐወ) ባስተማሩት መሰረት መሆን አለበት።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وَمَا آتاكم الرَّسُولُ فخذُوه وَمَا نهاكم عَنه فَانتَهوا وَاتَّقوا الله إنَّ الله شديدُ العِقاب ﴾ سورة الحشر .

*መልዕክተኛው የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ። አላህንም ፍሩ፤ አላህም ቅጣተ ብርቱ ነውና።(59:7)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : مَنْ عَمِلَ عَمَلاً لَيسَ عَلَيه أمرنا فَهوَ رَدُّ . رواه مسلم .

*የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) የኛ ፈቃድ ያልሆነን ነገር ያከናወነ ሰው ተግባሩ ውድቅ ነው። ሲሉ ተናግረዋል።* (ሙስሊም)

ጥ15. በአላህ ዘንድ እጅግ በጣም ከባድ የሆነው ወንጀል ምንድነው?

መ. በአላህ ዘንድ እጅግ በጣም ከባድ የሆነው ወንጀል በአላህ ማጋራት(ማሽረክ) ነው።

ሽርክ ማለት በአላህ ማጋራት ወይም በእሱ ላይ ሌላ አማልክትን ተጋሪ ማድረግ ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وإذ قَالَ لُقمانُ لابنه وَهو يَعظه يابُنَيَ لاَ تُشرِك بالله إنَّ الشِركَ لَظلمٌ عَظيم ﴾ سورة لقمان .

*ሉቅማንም: ለልጁ እርሱ የሚገሰፀው: ሲኾን:- ልጄ ሆይ! በአላህ(ጣኦትን) አታጋራ: ማጋራት ታላቅ በደል ነውና ያለውን (አስታውስ)።(31:13)*

**ሐዲስ**

وَلما سُئل رَسولُ الله صَلَّى الله علَيهِ وَسلَّمَ : أيُّ الذَّنبِ أعظَمُ ؟
قَالَ : أنْ ئجعَلَ لله نِداً ، وَهُوَ خلَقَكَ . البخاري ومسلم .

**የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ)** *''ከወንጀል ሁሉ የትኛው ነው ከባዱ?'' ተብለው በተጠየቁ ጊዜ እርሱ ብቻውን ፈጥ ሮ ሳለ ለአላህ አጋሪ ማድረግ ነው። ሲሉ መልሰዋል።*(ብይኻሩና ሙስሊም)

## ጥ16. እጅግ በጣም ከባድ የሆነ ማጋራት(ሽርክ) (ሽርክ አል-አክበር) ምንድነው?

መ. ሽርክ አል-አክበር ወይም እጅግ በጣም ከባድ የሆነ ሽርክ ማለት የአምልኮት ዘርፍ የሆኑ ሥራዎችንና ተግባሮችን ከአላህ ውጪ ለሌላ ማዋል ነው። እንዲሁም በህይወት የሌሉና በአቅራቢያችን የማይገኙትን ሰዎች እርዳታ መከጀል ከሽርክ አል-አክበር ይመደባል።

**ቁርአን እንዲህ ይላል:-**

﴿ وَاعبُدوا الله وَلاَ تُشرِكُوا به شيئاً ﴾ سورة النساء .

*አላህንም ተገዙ: በርሱም ምንንም አታጋሩ(4:36)*

**ሐዲስ**

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : مِنْ أكبَرِ الكَبائرِ الشرك بالله . رواه البخاري .

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) *በጣም አይከብድ ከከባዱ ወንጀሎች በአላህ ማጋራት ነው።* ሲሉ ተናገረዋል። (ቡኻሪ)

## ጥ17. በዘመኑ ሙስሊም ኅብረተሰብ ዘንድ ሽርክ አለን?

መ. አዎን፤ ሽርክ በሙስሊሞችም ዘንድ አለ። አላህም ይህንን አስመልክቶ በቁርአን እንደሚከተለው አስጠንቅቆናል።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وما يُؤمِنُ أكثَرُهُم بالله إلاّ وَهُم مُشرِكُونَ ﴾ سورة يوسف .

*አብዛኞቻቸውም: እነሱ አጋሪዎች ቸነው እንጂ በአላህ አያምኑም። (12:106)*

ሐዲስ

وَقالَ صَلَّى الله عَلَيه وَسَلَّم : لاتقوم الساعة حتى تلحق قبائلُ من أمتي بالمشركين وَحتى تُعبَدُ الأوثان . رواه الترمذي

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *ከሕዝቦቼ መካከል የተወሰኑት ብሄሮች ከሙሽርኮች ጋር ሳይቀላቀሉና ጣኦትንም ሳያመልኩ ሰዓቲ እንደማይደርስ ነው። ብለዋል(ትርሚዝ)*

## ጥ18. ሙታንን ወይም በአቅራቢያችን የሌሉቱን ሰዎች ዕርዳታ በመጠየቁ ላይ ያለው ኢስላማዊ ትዕዛዝ ምንድነው?

መ. በህይወት የሌሉትንም ሆነ በአቅራቢያችን የማይገኙትን ሰዎች ለመንፈሳዊና ለቁሳዊ ነገሮች እርዳታና ዕገዛ እንዲያደርጉልን መጠየቅ የሽርክ አል-አክበር ተግባር ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وَلاتَدعُ مِن دونِ الله مالا يَنفعكَ وَلا يَضُرُّك فإن فَعَلتَ فإنك

إذاً مِنَ الظَالمين ﴾ سورة يونس .
*ከአላህም በቀር የማይጠቅምንና የማይጎዳን አትግገዛ፡ ብትሰራም አንተ ያንጊዜ ከበደለኞቹ ትሆናለህ፡ (ተብያለሁ በላቸው)(10:106)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : مَن مات وَهو يدعو من دون الله نِدًّاً دَخَلَ النار . رواه البخاري .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክን አየፀለየና እያመለከ የሞተ እሳት ገባ።* ብለዋል።(ቡኻሪ)

ጥ19. ዱአዕ የኢባዳ አካል ነውን?

መ. አዎን ዱአዕ የኢባዳ አካል ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وَقال ربكم ادعوني أستَجِب لكم إنَّ الذينَ يَستَكبرون عن عِبادتي سَيَدخلونَ جهنم دَاخرين ﴾ سورة غافر

*ለምኑኝ፡ እቀበላችኋለሁና፡ እነዚያ እኔን ከመገዛት የሚኮሩት ፤ተወራዶች ኾነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ።(40:60)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : الدُعاء مُخُّ العِبادَة . رواه أحمد والترمذي .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *ዱዓዕ የኢባዳ ንጥረ ነገሩ ነው። ሲሉ ተናግረዋል።* (አህመድ፣ ቲርሚዚ)

ጥ20. ሙታን በሕይወት ያሉ ሰዎች ዕርዱን በማለት የሚያደርጉትን ጥሪ ይሰማሉን?

መ. አይሰሙም፤ በሕይወት ያሉሰዎች ዕርዱን በማለት የሚያደርጉትን ጥሪና ጥየቃ ሙታን አይሰሙም።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ إنك لاَ تُسمعُ الموتى ﴾ سورة النمل .

*አንተ ሙታንን አታሰማም:(27:80)*

﴿ وماأنت بمُسمعٍ مَنْ في القُبُور ﴾ سورة فاطر .

*አንተም፣ በመቃብር ውስጥ ያሉትን አሰሰሚ አይደለህም።(35:22)*

ጥ21. ከአላህ በስተቀር የማንንም፣ የምንንም ርዳታ መከጀል ይቻላልን?

መ. አይቻልም

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ إياك نعبد وإياكَ نستعين ﴾ سورة الفاتحة .

*አንተን ብቻ እንገዛለን፤ አንተንም ብቻ ርዳታን እንለምናለን። (1:5)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : إذا سَئَلتَ فاسئل الله وَإذا استعنتَ فاستعن بالله . رواه الترمذي .

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) *ማንኛውንም ነገር ለመጠየቅ ስትሻ አላህን ብቻ ጠይቅ፣ ርዳታም ሲያስፈልግህ ከአላህ ብቻ ተረዳ።* ብለዋል። (ቲርሚዚ)

## ጥ22. በአቅራቢያችን ካሉት ሰዎች ርዳታ መከጀል ይቻላልን?

መ. አዎን እነሱ ሊሰሩት በሚችሉት ነገር ላይ ርዳታና እገዛ እንዲያደርጉልን መጠየቅ እንችላለን።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وتعاونوا على البرّ والتقوى وَلاَ تعَاونوا على الإثم وَالعُدوان ﴾ سورة المائدة .

*በጎን ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፤ ግን በሐጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ።(5:2)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : والله في عَونِ العبدِ ماكَانَ العبدُ في عونِ أخيه . رواه مسلم .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *አላህ ባሪያውን በመርዳት ላይ ነው፣ ባሪያው ወንድሙን እስከተባበረ ድረስ* ብለዋል።(ሙስሊም)

## ጥ.23. ከአላህ በስተቀር ለሌላ ስለት ማድረግ ይቻላልን?

መ. ከአላህ በስተቀር ለማንም ስለት ማድረግ አይቻልም።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ رإذ قالت امرأةُ عِمرانَ ربّ اني نذرتُ لكَ مافي بطني محَرّراً ﴾ سورة آل عمران .

*የዒምራ ባለቤት(ሐና)፡- ጌታዬ ሆይ! እኔ በሆዴ ውስጥ ያለውን(ፅንስ ከሥራ) ነፃ የተደረገ ሲኾን ለአንተ ተሳልኩ፤ (አስታውስ)።* (3:35)

**ሐዲስ**

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : مَن نذَرَ أن يُطيع الله فَلْيُطِعه ، وَمَن نذَرَ أن يعصيَهُ فلاَ يَعصيه . رواه البخاري

**የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ)** *አላህን ለመገዛት የተሳለ ሰው ካለ ስለቱን ያሟላ፤ ለመወንጀል ከሆን ግን እንዳይፈፅም፡፡* **ብለዋል። (ቡኻሪ)**

**ጥ24. ከአላህ በቀር በሌላ እንስሳን መሰዋት ይቻላልን?**

**መ. አይቻልም! ለአላህ በስተቀር ለሌላ ተብሎ ወይም ከአላህ ስም ውጪ በሌላ እንስሳን መሰዋት (ማረድ) አይቻልም።**

**ቁርአን እንዲህ ይላል:-**

﴿ فصلِّ لربّك وانحر ﴾ سورة الكوثر .

*ስለዚህ ለጌታህ ስገድ፡ (በስሙ) ሰዋም። (108:2)*

**ሐዲስ**

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : لَعَنَ الله مَنْ ذَبَح لغير الله . رواه مسلم .

**የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ)** *ከአላህ ለሌላ ቁርባንን የሰዋ አላህ ረግሞታል።* **ብለዋል። (ሙስሊም)**

**ጥ25. መቃብርንመጠወፍ(መዞር) (ለምሳሌ የሞተውን ሰው ለመቃረብ ተብሎ) ይቻላልን?**

መ. አይቻልም። መቃብርን ወይም ማንኛውንም ሐውልት ወይም የትኛውንም ቦታ መጠወፍ አይቻልም። መጠወፍ(መዞር) የሚቻለው ከዓባን ብቻ ነው።

ቁርዓን እንዲህ ይላል:-

﴿ وليَطَّوفوا بالبيتِ العتيق ﴾ سورة الحج

*በጥንታዊውም ቤት (ከዓባ) ይዙሩ።(22:29)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : مَن طاف بالبيت سبعاً وَصَلى ركعتين كان كَعَتقِ رقبَةٍ . رواه ابن ماجه .

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) *በአላህ ቤት (በከዓባ) ሰባት ጊዜ የዞረና በመጨረሻም ሁለት ረከዓ የሠገደ: አንድ ባሪያ ነፃ እንዳወጣ ይቆጠርለታል*። ብለዋል። (ኢብን ማጃህ)

ጥ26. የጥንቆላ ተግባር በእስልም ና ይፈቀዳልን?

መ. የጥንቆላ ተግባር የኩፍር (የክህደት) ምልክት ስለሆነ ሙስሊሞች መፈፀም የለባቸውም።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ ومَا كَفَر سُليمَانُ وَلكِنّ الشّيَاطِينَ كَفَرُوا يُعلمُونِ النَاسَ السحرَ ﴾ سورة البقرة .

*ሱለይማንም አልካደም: (ድግምተኛ አልነበረም)፤ ግን ሰይጣናት ለሰዎችን ድግምትን የሚያስተምሩ ሲሆኑ ካዱ: (2:102)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : اجتَنبُوا السَبعَ الموبِقَاتِ : الشركُ بالله والسحرَ ... الخ : رواه مسلم .

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) *ለባት አደገኛ ወንጀሎችን ራቁ: ተጠንቀቁ: በአላህ ማጋራትን: መጠንቆልን... ወዘተ*፡ ብለዋል። (ሙስሊም)

ጥ27. በትንቢተኞችና የወደፊቱን የመተንበይ ችሎታ አለን በማለት በሚተነብዩት ሰዎችና በሚናገሩት ነገር ማመን እንችላለንን?

መ. በእነሱም ሆነ በሚናገሩት ነገር ማመን አንችልም::

ምክንያቱም የዓልጋይብ (ሚስጥርን) የማወቅ ችሎታ

ከአላህ በስተቀር ማንም አይኖረውምና።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ قُل لاَيعلمُ مَن في السمٰوات وَالأرض الغيبَ إلاّ الله ومَايَشعُرُون أيّانَ يُبعَثون ﴾ سورة النمل .

*በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ ሩቅን ምሥጢር አያውቅም: ግን አላህ(ያውቀዋል): መቼ እንደሚቀሰቀሱም አያውቁም: በላቸው። (27:65)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلّى الله عَليه وَسَلّم : مَنْ أتى عَرّافاً أو كَاهناً فَصَدَّقَه بما يقولُ ، فَقَد كفر بما أُنزِلَ على محمّد صَلى الله عليه وسلم . رواه أحمد .

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) *አዋቂ ነኝ ባይ ወይም ከጠንቋይ ዘንድ መጥቶ የጠየቀና የተነገረውንም እውነት ብሎ የተቀበለ በእርግጥ በሙሐመድ (ሰዐወ) በወረደው ቁርአን ክዷል*። ሲሉ ተናግረዋል። (አህመድ)

ጥ28. ምሥጢርን የማወቅ ችሎታ ማንም ሊሰጠው ይችላልን?

መ. አላህ ከመልዕክተኞቹ መካከል ሊገልጽላቸው ከሚፈልጋቸው በስተቀር ምሥጢርን የማወቅ ችሎታ ለማንም ሊሰጠው አይችልም። ከአሁን በኋላም ሌሎች መልክተኞች ከአላህ አይለኩም።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ عالم الغيب فلا يُظهر على غَيبه أحدًا إلا مَن ارتضى من رسُولٍ ﴾ سورة الجن

*(እርሱ) ሩቁን ምስጢር አዋቂ ነው: በምስጡሩም ላይ አንድንም አያሳውቅም። ከመልዕክተኛ ለወደደው ቢሆን እንጂ (ለሌላ አይገልጽም): (72:26-27)*

ጥ29. ከመንፈሳዊ: ከአእምሮ ወይም ከአካል በሽታ ወይም ከሌላ ጎጂ ነገር ይጠብቁናል በሚል እምነት፡ በአንገታችን፡ በእጃችን ወይም በሌሎችም የሰውነታችን ክፍሎች ላይ ክር: መዳብ ወይም ሌሎች ብረት ነክ ነገሮችን ማድረግ እንችላለን?

መ. አንችልም። በእንዲህ ዓይነቱ እምነት እነዚህን ነገሮች ማድረግ አንችልም። ምክንያቱም ከማናቸውም ጎጂ ነገሮች የሚጠብቀን አላህ ብቻ ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وإن يَمسَسك الله بضرٍ فلا كاشف له إلا هو ﴾ سورة الأنعام

*አላህም በጉዳት ቢነካህ፡ ለርሱ(ለጉዳቱ) ከእርሱ በቀር ሌላ አስወጋጅ የለም (6:17)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى اللهُ عَلَيهِ وَسَلَّم : أَمَّا إِنَّهَا فَلاَ تَزِيدُكَ إِلا وَهناً ، إِنبذها عَنكَ ، فَإِنَّكَ لَو مِتَّ مَاأَفلحتَ إِبداً . رواه الحاكم .

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) *ይህች መዳብ ይብሱኑ ድካም እንጂ ምንም አትጨምርልህም፤ ስለሆነም ወዲያ ወርውራት፤ እንተ ይችን እንደለበስክ ብትሞት ፍጹም ጭራሽ መዳኛ የለህም።* ሲሉ ተናግረዋል። (ሐኪም)

ጥ30. ከቡዳ ወይም ከማይታዩ ጎጂ ሐይሎች ይጠብቁናል በሚል እምነት ሉልወይንም: ቋጠሮ ነገር ማንጠልጠል ወይንም ዛጎል ወይም ማንኛውንም ብረት ነክ ነገር ማድረግ እንችላለን?

መ. ከአላህ መልካም ፍቃድ ውጪ ከማንኛውም ጎጂ ነገር ሊጠብቁን ስለማይችሉና ኢማናችንን ስለሚያደክሙ በዚህ ዓይነቱ እምነት እነዚህን ነገሮች ማድረግ የለብንም።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وإن يمسسك الله بضر فلا كاشف له إلا هو ﴾ سورة الأنعام .

*አላህም በጉዳት ቢነካህ፤ ለርሱ (ለጉዳቱ) ከእርሱ በቀር ሌላ አስወጋጅ የለም፤(6:17)*

ሐዲስ

وقَالَ صَلَّى اللهُ عَلَيهِ وَسَلَّم : مَن علَّق تميمةً فقد أشرَكَ . رواه أحمد

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ)*ቋጠሮ ነገር ያንጠለጠለ ሰው በእርግጥ በአላህ አጋራ።* ብለዋል። (አህመድ)

ጥ31. ከእስልምና ሕግ ውጪ በመፈፀምና በመኖር ሊደርስብን የሚችል ጉዳት ምንድን ነው?

መ. በአግራሞትነት ለሕብረተሰቡ ገንቢና ጠቃሚ ነው በሚል እምነት ማንም ሰው ከእስልምና ሕግ ውጪ የሚፈጽምና የሚኖር ከሆነ በርግጥ አድራጎቱ የክህደት ምልክት ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وَمَن لم يَحكم بما أنزلَ الله فأولٰئك هم الكَافرون ﴾ سورة المائدة .

*አላህም ባወረደው ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሓዲዎቹ እነርሱ ናቸው። (5:44)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلَيه وَسَلَّم : ومَالم تحكم أئمتُهم بكتاب الله ويتخيروا بما أنزل الله ، إلا جعلَ الله بأسَهم بينهُم . رواه ابن ماجه

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:- *መሪዎቻቸው በአላህ ኪታብ የማይፈርዱና ለእነሱ ሰዎች የሚመጥናቸውን ብቻ የሚተገብሩ እስካልሆኑ ድረስ በርሳቸው ብጥብጥ የሚያወርድባቸው ቢሆን እንጂ።* (ኢብን ማጀሕ)

ጥ32. አላህን ማን ፈጠረ በማለት ሸይጧን የሚያስነሳብንን ጥያቄ በምን መልኩ ነው ማስወገድ የምንችለው?

መ. እንዲህ አይነቱ የሸይጧን ተግባርና ክፉ ሐሳብ በአእምሮአችን በሚነሳበት ጊዜ፣ ሰውዬው እምነቱን በአንድ አላህ በማረጋገጥ፣ ከተረገመው ሸይጧን የአላህን ጥበቃ መሻት አለበት።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وإمَا يَنزَغَنَّكَ مِنَ الشيطَنِ نزغٌ فَاستَعِذ بِالله إنهُ سَميعٌ عَليم ﴾ سورة الأعراف .

*ከሰይጣንም (በኩል): ጉትጎታ ቢያገኝህ: በአላህ ተጠበቅ: እርሱ ሰሚው አዋቂው ነውና። (7:200)*

## ጥ33. ሽርክ አል-አክበር የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ምንድን ናቸው?

መ ሽርክ አል-አክበር እጅግ በጣም ከባድና ምህረት የማይደረግለት ወንጀል ነው። ይህም ማለት ሰውዬው በሕይወቱ እያለ ለወንጀሉ(ለማጋራቱ) አላህን ምህረት ሳይጠይቅ የሞተ እንደሆነ ለዘለአለም በጀሐነም እሳት ውስጥ እንዲቆይ የሚያደርግ ወንጀል በመሆኑ ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ إنَهُ مَن يُشرِك بِالله فَقَد حَرَّم الله عَلَيه الجَنَّةَ ومَأواهُ النَّارُ وَمَا للظَّالِمينَ مِن أنصَار ﴾ سور المائدة .

*በአላህ የሚያጋራ ሰው፣ አላህ በርሱ ላይ ገነትን በርግጥ እርም አደረገ፤ መኖሪያውም እሳት ናት ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የላቸውም። (5:72)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلَيه وَسَلَّم : وَمَن لَقيَ الله يُشرِك به شيئاً دَخلَ النارَ . رواه مسلم .

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) *የሽርክን ተግባር እያከናወነ*

*አላህን የተገናኘ ሰው ጀሀነም ገባ።* ሲሉ ተናገረዋል።
(ሙስሊም)

ጥ34. የሽርክን ተግባር የሚፈፅመውን ሰው:

በጎ ስራው ይጠቅመዋልን?

መ. የሽርክን ተግባር የሚያከናውን ሰው መልካም

ሥራው አይጠቅመውም፤ በአላህ ዘንድም ተቀባይነት
የለውም።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وَلَو أشرَكوا لحَبِطَ عنهُم مَاكَانوا يَعلَمون ﴾ سورة الأنعام

*ባጋሩም ኖሮ ይሰሩት የነበሩት ከነሱ በታበሰ ነበር(6:88)*

ጥ35. ሽርክ- አል አስጋር (መለስተኛው ሽርክ)

ምንድን ነው?

መ. ሽርክ -አል አስጋር (መለስተኛው ሽርክ) ማለት የይዩልኝ ስራ ነው። አንድ ሰው አምልኮትን ወይንም በጎ ስራን ሙሉ በሙሉ በጥራትና በታማኝነት ለአላህ ብሎ ማከናወን አለበት፤ ነገር ግን ሰውዩው ሌላ ጥቅምን የሚሻ ሆኖ ሲገኝ መለስተኛው ሽርክ ይሆናል።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ فَمَن كَانَ يَرجوا لِقَاء ربّهِ فَليَعمل عَملاً صَالحاً ولا يُشرك بعِبادةِ ربّه أحَداً ﴾ سورة الكهف

*የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው: መልካም ሥራን ይሥራ: በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ: በላቸው። (18:110)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : إنَّ أخوَف مَاأخاف عليكم الشرك الأصغر : الرياء . رواه أحمد .

የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) *ለእናንተ ከምፈራው ነገር ሁሉ ይበልጥ የምፈራው ቢኖር መለስተኛውን ማጋራት ነው፤ (እሱም ለይዩልኝ ኢባዳ ማድረግ ነው)*::ብለዋል። (አህመድ)

**ጥ36. ከአላህ ሥም በስተቀር በሌላ መማል ይፈቀዳልን?**

መ. አይፈቀድም! በአላህ ስም በስተቀር በማንም: በምንም ስም መማል አይፈቀድም።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

*<u>በቁርአን ውስጥ ሁሉም መልእክተኞች የማሉት በአላህና በባህሪያቱ ነው።</u>*

ሐዲስ

، وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : مَن كَانَ حَالفاً فليحلف بالله أو ليصمت . البخاري ومسلم .

የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) *መማል የሚፈልግ ሰው በአላህ ብቻ ይማል፤ አለበለዚያ ዝም ይበል።* ሲሉ ተናግረዋል። (ቡኻሪና ሙስሊም)

وَقَالَ صَلَّى الله عَلِيه وَسَلَّم : مَن حَلَف بِغير الله فَقَد أشرَك . رواه أحمد .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *ከአላህ ሌላ በሌላ የማለ በርግጥም አጋርቷል።* ብለዋል። (አህመድ)

ጥ37. አላህን ማንኛውም ነገር በምንጠይቅበት ጊዜ ምን ዓይነት ተወሱል ወይም ወሲላ(ማግለጃ) መጠቀም እንችላለን?

መ. ተወሱል ወይም ወሲላ ማለት ከፍ ያለ ልመና ነው። በተለምዶ ሰዎች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የሰዎችን ማዕረግ፣ ክብር እና ዝና በመጠቃቀስ ሲለምኑ እንሰማለን። እንደዚሁም አንዳንድ እምነታቸው ደካማ የሆኑ ሰዎች አላህን ለፍላጎታቸውና ለምኞታቸው ሲማፀኑ የነብያችን ሙሐመድ (ሰዐወ) ማዕረግ፣ ክብር ዝናና መልካም ሥራን እንደማግለጃ ይጠቀሙበታል።

በቁርአንና በሱና መሠረት ሁለት ዓይነት ተወሱል

(ማግለጃ) ይኖራል። እነሱም:-

1. የተፈቀደ ወሲላ ወይም ተወሱል:

2. የተከለከለ ወሲላ ወይም ተወሱል:

ጥ38. የተፈቀደ ወሲላ ወይም ተወሱል ምንድን ነው?

መ. አላህን በተፈቀደው ወሲላ ማግለድ እንችላለን። ይህም አላህን በምንለምንበት ጊዜ የእሱን የውዳሴ ስሞችና መልካም ባህሪያቱን፣ ግሐሪና አዛኝ መሆኑን በመጠቃቀስ የምናደርገው ዒባዳ ነው።

**ቁርአን እንዲህ ይላል:-**

﴿ وللهِ الأسمَاءُ الحُسنَى فَادعُوهُ بِهَا ﴾ سورة الأعراف

*ለአላህም መልካም ስሞች አሉት፤ (በተፀልዩ) በርሱም ጥሩት፤(7:180)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى اللهُ عَلَيهِ وَسَلَّم : أسألُكَ بكل اسمٍ هوَ لكَ . رواه أحمد .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *ዱአእ ሲያደርጉ እንዲህ ብለዋል:- የአንተ በሆነ ስም ሁሉ እማፀናለሁ፡፡* (አህመድ)

* መልካም ሥራዎቻችንንም በመጠቃቀስም አላህን መለመን ይቻላል።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ ياأيُّها الَّذينَ آمَنوا اتَّقُوا الله وابتَغُوا إلَيهِ الوَسِيلَةَ ﴾ سورة المائدة .

*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ: ወደርሱም መቃረቢያን(መልካም ሥራን) ፈልጉ: (5:35)*

በላይኛው አያሕ (አንቀጽ) የተጠቀሰው "መጠጊያ መንገድ" ወደ አላህ መቅረብና መጠጋት የምንችለው በሰራነው መልካም ሥራ ነው፤ አላህ "ጸርሱ መንገድ መታገል" ወይም ጅሐድ መልካም ሥራ መሆኑን ጠቅሷታል ወደ አላህ መቃረቢያ መንገድም ነው።

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى اللهُ عَلَيهِ وَسَلَّم للصَحابي الذي سأله مُرافَقَتَه الجَنَّةَ : أعِنّي عَلَى نَفسِكَ بِكَثرَةِ السُّجُود . رواه مسلم .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *በጀነት የእርሰ ጎረቤት እሆን ዘንድ ተባበሩኝ ላላቸው ሳሐቢህ መልስ ሲሰጡ: ሰላት በማብዛት እርዳኝ፡* ብለዋል። (ሙስሊም)

*ማስታወሻ:- የምንፈልገውን ነገር ለማግኘት ሰላትን በማብዛት መሆኑ ተገልፀዋል። ይህም መልካም ሥራ መሆኑን ያመለክታል።

**ሐዲስ**

كقصةِ أصحَاب الغَارِ الّذِين تُوسَلوا بأعمَالِهم الصالِحة فَفَرّجَ آللّه عَنهم . رياض الصالحين :

*የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) ዋሻ የተዘጋባቸው ሶስት ግለሰቦች ቀደም ሲል ባከናወኑት መልካም ሥራ ጌታቸውን አማፀኑት ለምነው መገላገላቸውን ነግረውናል። (ሪያዱ ሷሊሂን)*

## ጥ39.፡ የተከለከለው ወሲላ ወይም ተወሱል ምንድን ነው?

1. ወደ መልካም ሰዎች መቃብር በመሄድ ፍላጎታችንና ምኞታችንን እንዲያሟሉልን መለመን:
2. አላህን ለማግለድ ማንነታቸውን መጠቀም:
3. በሕይወት የሌሉትን ሰዎች ዕርዳታ መከጀል:

**ቁርአን እንዲህ ይላል:-**

﴿ ولاتَدعُ مِن دون الله مَالاَ يَنفَعُك وَلاَ يَضُرُّكَ فإن فَعَلتَ فإنّك إذاً مِنَ الظّالِمين ﴾ سوُرة يونس .

*ከአላህም በቀር የማይጠቅምንና የማይጎዳን አትግገዛ፤ ብትሰራም አንተ ያን ጊዜ ከበደለኞቹ ትሆናለህ: (ተብያለሁ: በላቸው)። (10:106)*

## ጥ40. በሐይማኖት ውስጥ ቢዳዓ ምንድን ነው?

መ. ጠቃሚ ነው ተብሎ በሐይማኖት ውስጥ የተጨመረ ነገር ቢዳዓ (የዲን ፈጠራ) ይባላል።

**ቁርአን እንዲህ ይላል:-**

﴿ أم لَهُم شُرَكَاءُ شَرَعُوا لَهُم مِنَ الدّين مَالَم يَأْذن بِهِ الله ﴾ سورة الشورى .

*ከሐይማኖት አላህ በርሱ ያልፈቀደውን ለነርሱ የደነገጉ ተጋሪዎች: (42:21)*

**ሐዲስ**

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : مَن أحدث في أمرنا هذا مَالَيسَ منه فهو ردّ . رواه البخاري ومسلم .

**የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ)** ***በዲናችን አግባብ የሌለውን ነገር የፈጠረ ወይም የጨመረ እርሱ ውድቅ ነው።*** **ብለዋል።** **(ቡኻሪና ሙስሊም)**

**ጥ41. በመልዕክተኛው (ሰዐወ) ማዕረግና ክብር ማማለድ ለምሳሌ ሰውዬው እንዲህ ቢል ''ጌታዬ ሆይ! በመልዕክተኛው ሙሐመድ(ሰዐወ) ማዕረግና ክብር ብለህ እንድትፈውሰኚ እለምንሃለሁ።" ማለት ይፈቀዳልን?**

**መ. እንዲህ አይነቱ ወሲላ ቢደዓ ነው። አላህ እንዲህ ዓይነቱን ወሲላ የተጠቀመ መልዕክተኛ ወይም መልካም ሰው በቁርአን ውስጥ እንደ ምሳሌ አልጠቀሰም:: በተጨማሪም ሳሐቢዎች እንዲህ ዓይነቱን ወሲላ ለመጠቀማቸው ምንም ዓይነት ማረጋገጫ የለም።**

**ጥ42. አላህን በሕይወት ባሉት ወይም በሞቱት መልካም ሰዎች ማዕረግና ክብር ማማለድ ይፈቀዳልን?**

**መ. እንዲህ ዓይነቱ ወሲላ ወይም ተወሱል ቢዳዓ ነው። አላህ**

እንዲህ አይነቱን ወሲላ የተጠቀመ መልዕክተኛ:: መልካምና ሓይማኖተኛ የሆነ ሰውን እነደምሳሌ አልጠቀሰም። በተጨማሪም ሳሐቢዎች የዚህ ዓይነቱን ወሲላ ለመጠቀማቸው ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም።

## ጥ43. ዱዓእ በአላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ የሰዎችን አማላጅነት ያስፈልገዋልን?

መ. አያስፈልገውም! ዱዓእ በአላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ የማንንም አማላጅነት አያስፈልገውም፤ ምክንያቱም አላህ ለማንም በጣም ቅርብና ሁሉንም ሰሚ ነውና።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ وَإِذَا سَأَلَكَ عِبَادِي عَنِّي فَإِنِّي قَرِيبٌ أُجِيبُ دَعْوَةَ الدَّاعِ إِذَا دَعَانِ ﴾ سورة البقرة .

*ባሮቹም ከኔ በጠየቁህ ጊዜ: (እንዲህ በላቸው):- እኔ ቅርብ ነኝ: የለማኝን ፀሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ: (2:186)*

## ጥ44. በሕይወት ያለውን ሰው ዱዓዕ አድርግልኝ ብሎ መጠየቅ ይቻላልን?

መ. ማንኛውም ሙስሊም ሌላውን ሙስሊም ዱዓዕ አድርግልኝ ብሎ መጠየቅ ይችላል። ሰሓባዎችም ሆኑ መልዕክተኛው(ሰዐወ) ዱዓዕ እንዲደራረጉ ይጠያየቁ ነበር።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ خُذْ مِنْ أَمْوَالِهِمْ صَدَقَةً تُطَهِّرُهُمْ وَتُزَكِّيهِمْ بِهَا وَصَلِّ عَلَيْهِمْ إِنَّ صَلَوٰتَكَ سَكَنٌ لَهُمْ وَاللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴾ سورة التوبة .

*ከገንዘቦቻቸው ስትኾን በርሷ የምታጠሬቻውና የምታፋፋቸው የኾነችን: ምፅዋት ያዝ: ለነሱም ፀልይላቸው፤ ፀሎትህ ለነሱ እርካታ ነውና፤ አላህም ሰሚ አዋቂ ነው።(9:103)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : دُعَاء المُسلِم لأخيِهِ المسلم في ظَهر غَيبِهِ لاَيُرد . رواه مسلم .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *ሙስሊም ለሙስሊም ወንድሙ በርቀት የሚያደርግለት ፀሎት በርግጥ አይወድቅም።* ብለዋል።(ሙስሊም)

ጥ45. መልዕክተኛው (ሰዐወ) በፍርድ ቀን(የውማልቅያማ) አማላጅ ከሚሆኑላቸው ሰዎች እንዴት መሆን እንችላለን?

መ. የመልዕክተኛውን (ሰዐወ) አማላጅነት ለማግኘት ተስፋ የምናደርገው አላህንና መልዕክተኛውን (ሰዐወ) በሕይወታችን እስካለን ድረስ በመታዘዝ ነው። አላህ የመልእክተኛውን(ሰዐወ) ሸፋዓ እንዲሰጠን በመለመን ጭምር ነው። ይሁን እንጂ ከአላህ ፍቃድ ውጪ ማንም ሸፋዓ ሊያደርግ አይችልም።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ أم اتَّخذوا مِن دُون الله شُفَعَاء ، قُل أَوَلَو كَانوا لاَيملكون شَيئاً ولاَ يَعقِلُون . قُل لله الشَفَاعَةُ جَميعاً ﴾ سورة الزمر .

*ከአላህ ሌላ አማላጆችን ያዙ: አነርሱም ምንንም የማይችሉና የማያውቁ ቢኾኑም? በላቸው። ምልጃ መላውም የአላህ ብቻ ነው፤ (39:43-44)*

ጥ46. የመልዕክተኛው(ሰዐወ) ምልጃ (ሸፌዓ) ምን ዓይነት ነው?

መ.የመልዕክተኛው (ሰዐወ) ሸፌዓ አላህ በፍርዱ ቀን አድርግ ብሎ በሚያዛቸው ልዩ በሆነች ዱዓዕ አማካይነት የሚከናወን ነው።

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى اللهُ عَلَيهِ وَسَلَّم : إنّي أختَبأتُ دَعوَتي شَفَاعَةً يَومَ القِيَامَةِ لِمَن مَاتَ مِن أُمّتِي لاَيُشرِكُ بالله شَيئاً . رواه مسلم .

*የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) መቅረቢያ የሌላት ፀሎት ከሁሉም በአላህ ምንም ላላጋሩት መሸምገያ እና ቅጣት ማዳኛ ትሆንላቸው ዘንድ ቀጥባላቸዋለሁ ብለዋል። (ሙስሊም)*

**ጥ47. መልዕክተኛውን (ሰዐወ) ከመጠን በላይ ማሞገስና ማጋነን ይቻላልን?**

**መ. እንደዚህ ማድረግ አይቻልም። የመልእክተኛው (ሰዐወ) ማዕረግ: ክብር: ባህሪ: ፀባይ እና ጥሩ ምግባራቸው በቁርአንና በሐዲስ በደንብ ተገልጾዋል። ሙስሊሞች በነዚህ ሁለት ምንጮች በተገለፁት መሰረት ራሳቸውን ቀጥ በማድረግ አለባቸው። ከሰው ዘር ሁሉ ምርጥ ሰው የተባሉ ናቸው። ነገር ግን.እርሳቸውን በማመስገን ላይ ማጋነን በእርሳቸውና በአላህ መካከል ሚዛን አለመጠበቅ በአቂዳችን ላይ ችግር ስለሚያመጣና ደካማ ኢማን ያላቸውን ሰዎች ከመንገድ ስለሚያወጣ መጠንቀቅ አለብን።**

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ قُل إنّما أنَا بَشَرٌ مِثلُكُم يُوحَى إلَيّ أنّمَا إلٰهُكُم إلٰهٌ وَاحِدٌ ﴾ سورة الكهف .

*እኔ እምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት: ወደኔ የሚወርድልኝ ቢጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ: በላቸው። (18:110)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى اللهُ عَلَيهِ وَسَلَّم : لاتُطرُوني كَمَا أطرَتِ النَصَارَى عِيسى ابنِ مَريم ، فإنّمَا أنَا عَبدٌ فَقولُوا عَبدُ الله وَرَسُولُه . رواه البخاري .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *ከርስቲያኖች የማረያምን ልጅ፡- ዒሳ እንዳጋነኑት ሁሉ እታጋንኑኝ፤ እኔ የአላህ " ቀን አገልጋይና" " ታማኝ፡ መልዕክተኛው" ስለሆንኩኝ በዚህ መልክ ብቻ ጥሩኝ።* ብለዋል። (ቡኻሪ)

ጥ48. ዊላ ምንድን ነው?

መ. የሙዕሚኖች ለአንድ አላህ ብለው መዋደድ፡ መፈቃቀር መተባበርና መረዳዳት ዊላ ይባላል።

ቁርአን እንዲህ ይላል?

﴿ وَالمؤمنون وَالمؤمنات بَعضُهم أولياء بَعض ﴾ سورة التوبة

*ምእምናንም ምእምናትም፡ ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፡ (9:71)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : المؤمِن للمؤمِن كالبُنيان يَشُد بَعُضه بَعضاً . رواه مسلم .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *አማኞች እንደ ህንፃ ድንጋዮች ይደጋገፋሉ።* ብለዋል። (ሙስሊም)

ጥ.49 ወሊየአላህ ማን ነው?

መ. ትክክለኛ አማኝ ነው። አላህን ሁል ጊዜ የሚፈራ ነው። ግዴታዎቹን አላህ ባዘዘውና መልዕክተኛው (ሰዐወ) ባስተማሩት መሠረት የሚያከናውን ነው። ፍጥረታትን ሁሉ በነቢያችን ሙሐመድ (ሰዐወ) ላይ በወረደው ቁረአን መሰረት የሚያስተናግድ ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ ألاَ إنّ أولياءَ الله لأخوف علَيهم وَلا هم يحَزنون الذين آمنوا وَكانوا يَتّقون ﴾ سورة يونس .

*ንቁ: የአላህ ወዳጆች፣ በነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም። (እነሱም) እነዚያ ያመኑትና ይፈሩት የነበሩት ናቸው። (10:62-64)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : إنّما وَلِيّي الله وَصَالح المؤمنين . رواه أحمد .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *የኔ ወገኖች አላህና ትክክለኛ አማኞች ብቻ ናቸው።* ብለዋል። (አህመድ)

ጥ50. ሙስሊሞች መምራትና መፍረድ ያለባቸው በምንድን ነው?

መ. ሙስሊሞች በሙሉ መምራትና መፍረድ ያለባቸው በቁርአንና በትክክለኛው ሐዲስ መሆን አለበት።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ فاحكم بَينَهم بِمَا أنزل الله ولاَ تَتّبع أهَواءَهم عَمَّا جَاءكَ مِنَ الحَق ﴾ سورة المائدة .

*በመካከላቸውም፡ አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ፤ እውነቱም ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል። (5:48)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : عَالِم الغيب وَالشهادة أنتَ تَحكم بَينَ عِبَادَك . رواه مسلم .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *ሩቅና ቅርብን አጣምረህ የምታውቀው በባሮችህ መካከል ፍትህ የምታሰፍነው አንተው ብቻ ነህ። ሲሉ ተናገረዋል።* (ሙስሊም)

## ጥ51. አላህ ቁርአንን ያወረደው ለምን አላማ ነው?

መ. አላህ ቁርአንን ያወረደው ምእመናን እንዲያነቡት፣ እንዲገነዘቡት፣ እንዲሰሩበትና እንዲመሩበት ነው።

**ቁርአን እንዲህ ይላል:-**

﴿ اتبعوا مَاأُنزل إلَيكم مِن رَبكم وَلاَتتبِعوا مِن دونه أولياء ﴾ سورة الأعراف .

*ከጌታችሁ ወደናንተ የተወረደውን ተከተሉ፡ ከአላህም ሌላ ረዳቶችን አትከተሉ፡ (7:3)*

**ሐዲስ**

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : إقرَأوُا القُرآن وَاعمَلُوا بهِ وَلاتَأكُلوا بهِ . رواه أحمد .

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) *ቁርአንን ተማሩና ሥሩበት እንጂ ማታለያና መብሊያ አታድርጉት።* ሲሉ ተናግረዋል። (አህመድ)

## ጥ.52 ትክክለኛውን ሐዲስ በተመለከተ ያለው ትዕዛዝ ምንድን ነው?

መ. በትክክለኛው ሐዲስ የተጠቀሱትን ማናቸውንም ነገር ማመንና በሥራ መተርጎም የማንኛውም ሙስሊም ግዴታ ነው።

**ቁርአን እንዲህ ይላል:-**

﴿ وَما آتاكم الرسُول فَخذوه وَمَا نَهاكُم عَنه فَانتَهوا ﴾ سورة الحشر .

*መልዕክተኛውም የሰጣችሁን(ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ። (59:7)*

**ሐዲስ**

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : عَلَيْكُم بِسُنَّتي وَسنةِ الخُلَفاء الرَاشِدين المَهديين ، تمَسكوا بِها . رواه أحمد .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *የኔንና የቅን ምክትሎቼን ፈለግ ተከተሉ: እሱንም በእጅጉ አጥብቃችሁ ያዙ።* ብለዋል። (አህመድ)

ጥ53. በሐዲስ ሳናምን ቁርአንን ብቸኛ መመሪያ አድርጎ ማመን በቂ ነውን?

መ. አይደለም! ትክክለኛውን ሐዲስ ሳናምንና ሳንቀበል በቁርአን ብቻ መሥራት አንችልም። መልዕክተኛው (ሰዐወ) የተናገሩትና የሰሩት ከተገለፀው ውስጥ ይመደባልና።

**ሐዲስ**

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : ألا وَإنِي أُوتِيتُ القُرآن وَمِثلَه مَعَهُ رواه أبو داود .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *ንቃ ብላችሁ ስሙኝ! እኔ ቁርአንና የሱን መሰል ተሰጥቻዋለሁ።* ብለዋል።(አቡዳውድ)

ጥ54. የአላህን ውሳኔና የመልዕክተኛውን ትዕዛዝ በመተው የትክክለኛ ኢማሞችንና የሙስሊም ምሁራንን አስተያየት መቀበል ይቻላልን?

መ. የአላህን ውሳኔና የመልዕክተኛውን ትዕዛዝ የሚቃረን የማንንም አስተያየት ወይም ሐሳብ መቀበል አንችልም።

**ቁርአን እንዲህ ይላል:-**

﴿ ياأيها الذينَ آمَنُوا لاتُقَدِمُوا بَينَ يَدَيِّ لله وَرَسُولِه ﴾ سورة الحجرات .

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልዕክተኛው ፊት (ንፍሶቻችሁን)አታስቀድሙ፡ (49:1)

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : لاطَاعةَ لِمَخلُوق في مَعصيَةِ الخالِق .

رواه الطبراني .

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) የፈጣሪን ፍቃድ ጥሶ ፍጡርን ማገልገል የለም። ሲሉ ተናግረዋል(ጣብራኒ)

ጥ55. ሙስሊሞች ልዩነቶቻቸውን በምን መልኩ ነው የሚያስወግዱት?

መ. ሙስሊሞች በማናቸውም ነገር ላይ በተከራከሩ ጊዜ ወደ አላህ መጽሐፍና ወደ መልዕክተኛው (ሰዐወ) ትክክለኛ ሱና መመለስ አለባቸው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ فإن تَنازَعتُم في شَيءٍ فَردّوه إلى الله وَالرَّسُول إن كُنتم تُؤمِنون بالله وَاليَوم الآخر ذَلِكَ خَيرٌ وأحسَن تأويلا ﴾ سورة النساء .

በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትኾኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና መልዕክተኛው መልሱት፤ ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው።(4:59)

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : عَلَيكم بِسُنَتي وَسُنةِ الخُلَفاء الراشِدين المَهدِيين تَمَسَكُوا بِها . رواه أحمد .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *የዷና የቅን ምክትሎቼን ፈለግ ተከተሉ እሱንም በእጅጉ አጥብቃችሁ ያዙ።* ብለዋል። (አህመድ)

## ጥ56. ለአላህና ለመልእክተኛው (ሰዐወ) ውዴታችን ን በምን መልኩ ነው የምንገልፀው?

መ. ለአላህና ለመልዕክተኛው (ሰዐወ) ያለንን ውዴታ የምንገልጸው አላህንና መልክተኛውን በመታዘዝና ያዘዙትንም በመሥራት ነው።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ قُل إنْ كُنتُم تُحبون الله فَاتَّبِعونِي يُحبِبكُم الله وَيَغفِرُ لَكُم ذُنوبَكم والله غَفورٌ رَحيم ﴾ سورة آل عمران .

*በላቸው:- አላህን የምትወዱ እንደኾናችሁ: ተከተሉኝ: አላህ ይወዳችኋልና: ኀጢአቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና: አላህም መሐሪ አዛኝ ነው። (3:31)*

ሐዲስ

وَقَالَ صَلَّى الله عَليه وَسَلَّم : لايُؤمِن أحَدَكُم حَتَى أكُونُ أحَب إليه مِن والِده وَوَلَدِهِ وَالناسِ أجمَعين . رواه البخاري ومسلم .

የአላህ መልዕክተኛ(ሰዐወ) *ከናንተ ማንኛውም ትክክለኛ አማኝ አይሆንም: እኔን ከወላጅና ከልጁ ባጠቃላይ ከማንም ሰው ይበልጥ ተወዳጅ እስከ ምሆንበት ድረስ።* ሲሉ ተናግረዋል።

(ቡኻሪና ሙስሊም)

ጥ57. ቢድዓ ሐሳናህን በተመለከተ በእስልምና ያለው ትእዛዝ ምንድን ነው።

መ. ቢደዓ ሐሳናህ በእስልምና የለም። ቢዳዓ የተባለ በሙሉ አዲስ የተፈጠረ ነገር ነው፤ ተቀባይነትም አይኖረውም።

ቁርአን እንዲህ ይላል:-

﴿ اليَومَ أكمَلتُ لَكُم دِينَكُم وَأتمَمْتُ عَليكُم نِعمَتي وَرَضيتُ لَكُم الإسلامَ ديناً ﴾ سورة المائدة .

*ዛሬ ሐይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ፀጋዬንም በናንተ ላይ ፈፀምኩ። ለእናንተም እስልምናን ከሐይማኖት በኩል ወደድኩ።(5:3)*

ሐዲስ

وَقالَ صَلّى الله عَليه وَسَلَّم : كُلُّ بِدعَة ضَلالَة وَكُلُّ ضَلالَة في النّار . رواه أحمد .

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) *በዲን በኩል ፈጠራ የተባለ ሁሉም ጥመት ነው፤ ጥመትም ሁሉ መውደቂያው እሳት ነው።* ብለዋል። (አህመድ)

# أصـول الـعقيدة

اللغة الأمهرية (أثيوبيا)

ترجمة

عبدالناصر عبدالله أحمد

إصدار

المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بالمعذر وأم الحمام

تحت إشراف وزارة الشؤون الإسلامية والأوقاف والدعوة والإرشاد

ت: ٤٨٢٦٤٦٦ فاكس: ٤٨٢٧٤٨٩ ص.ب: ٣١٠٢١ ، الرياض: ١١٤٩٧

١٩